አዲስ ዘመን ሰኞ ሰኔ 10 ቀን 2016 ዓ.ም

# ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል

## ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

# የአንጋፋዎቹን ዱካ እየረገጡ ያሉት ተተኪ ወጣቶች

ኢያሱ መሰለ

የአንድ ተቋም የመፈጸም አቅም ቀጣይነት እንዲኖረው ከሚያስችሉ ጉዳዮች አንዱ የነባርና አንጋፋ ሙያተኞችን እግር የሚተኩ ወጣት ባለሙያዎችን ማፍራት ነው:: ከዚህ አንጻር የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ወጣት ሠራተኞቹን ከአንጋፋዎቹ ጋር በማቆራኘት ልምድ እየቀሰሙ የነገ የተቋሙና የሀገር ተስፋ እንዲሆኑ እያበቃቸው ይገኛል:: እኛም በዛሬው ዝግጅታችን በግልገል ጊቤ-2 ኃይል ማመንጫ ጣቢያ በተለይም በጥገና እና ኦፕሬሽን ክፍሎች ዐሻራቸውን እያስቀመጡ ስላሉ ወጣት መሃንዲሶች ያዘጋጀነውን ጽfከፍ ልናስነብባችሁ ወድደናል::

የግልገል ጊቤ 2 ኃይል ማመንጫ ጣቢያ ባለፉት ተከታታይ ዓመታት ካከናወናቸው የጥገና ሥራዎች መካከል የሶስት ተርባይን ኖዝሎችን ቀይሮ በሙሉ አቅማቸው ኃይል እንዲያመርቱ ያስቻለው ሥራው ከሁሉም በላይ ተጠቃሽ ነው:: የመለዋወጫ እቃዎችን ተጠግነው ዳግም ለአገልግሎት እንዲውሉ የሚደረገውም ጣቢያው ባደራጀው ወርክሾፕ ውስጥ ነው:: በዚህ በወርክ ሾፕ ውስጥ ታዲያ ለጥገና ሥራው ግብዓት የሚሆኑ ቁሳቁስ በአንጋፋና ወጣት ባለሙያዎች ርብርበ አስፈላጊውን ቅርጽ ይዘው እንዲወጡ ይደረጋል:: ለጥገና ሥራው የሚያስፈልጉ ቁሶችን በማከሙም ይሁን የታከሙትን በመግጠሙ ሂደት ወጣት ባለሙያዎቹ የአንጋፋቹን ዱካ እየተከተሉ የሚሠሩት ሥራ ቀላል ግምት የሚሰጠው አይደለም:: ለአብነት እንመልከታቸው::

ወጣት መሃንዲስ ፈንታሁን እስከዚያው ከባህርዳር የኒቨርሲቲ በ2011 ዓ.ም በመካኒካል ኢንጂነሪንግ ተመርቆ ከ2013 ዓ.ም ጀምሮ በግልገል ጊቤ-2 ኃይል ማመንጫ ጣቢያ ጥገና ክፍል ውስጥ የሚሠራ ባለሙያ ነው:: በወርክ ሾፕ ውስጥ በሚገኙ የሌዝ ፣ የሜሊንግ ፣ የስሎቲንግና የፕረሲንግ ማሽኖች ላይ ለጥገና ሥራ ግብዓት







ፎቶ ዋሲሁን ታደሰ

ፈንታሁን እስከዚያው

መልካም ባወቀ

ሳሙኤል ንጉሴ

የሚሆኑ መለዋወጫ እቃዎችን ሲያስተካክልና ቅርጽ ሲያሲዝ አግኝተነዋል:: ብሎኖችን ፣ ሲሊንደር ቅርጽ ያላቸውንና ጠፍጣፋ ብረቶችን ፤ የመጠረብ፣ የመቁረጥ ፣ መጠናቸውን የመቀነስ ፣ የመቦርቦር ፣ ጥርስ የማውጣት፣ የመብሳት ፣ ሥራዎችን ይሠራል:: በአፈር እና በጠጠር የተበሉ ኖዝሎች የመጀመሪያውን ቅርጻቸውን እንዲይዙም በዚሁ ክፍል ውስጥ ይታከማሉ:: ወጣቱ ማሃንዲስ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይልን ከተቀላቀለ በኋላ በቲዮሪ የተማረውን ትምህርት በተግባር የመተርጎም እድል ማግኘቱን ይናገራል:: ባለፉት ሶስት ዓመታት ከአንጋፋ ባለሙያዎች ልምድና አዳዲስ እውቀት እያገኘ ስለመሆኑንም ያስረዳል:: ባገኘው ልምድም በተርባይኖች ጥገና ላይ ዐሻራውን አሳርፏል::

ሌላዋ ወጣት መሃንዲስ መልካም ባወቀ ትባላለች:: በ2013 ዓ.ም ከባህርዳር ዩኒቨርሲቲ በመካኒካል ማሃንዲስነት ተመርቃ ከመስከረም 2015 ዓ.ም ጀምሮ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይልን እንደተቀላቀለች ትናገራለች:: በግልገል ጊቤ 2 ኃይል ማመንጫ ጣቢያ የጥገና ክፍል ሠራተኛ ሆና ተመድባ መሥራት ከጀመረች ገና አንድ ዓመት ከስድስት ወሯ ነው:: በዚህ አጭር ጊዜ ታዲያ በርካታ ልምዶችንና እውቀቶችን እንዳካበተች ትናገራለች::

በማሺኖች ላይ ከሚደረገው እለታዊ፣ ሳምንታዊ፣ ወርሃዊና ዓመታዊ ቁጥጥር ጋር ተያይዞ የፕሪቬንቲቭና ኮሬክቲቭ ጥገናዎች ላይ ትሳተፋለች:: የጥገና ሥራዋ ስላማሽኖች አጠቃላይ አካል ክፍል ለማወቅ በእጅጉ እንደረዳትም ትገልጻለች:: መልካም፤ ዘወትር በምታከናውናቸው የጥገና ሥራዎች ልምድና ጠለቅ ያለ አዳዲስ እውቀት ማግኘቷን ታስረዳለች::

በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ውስጥ የሚሠሩት ውስን ሴት መሃንዲሶች እንደሆኑ የተናገረችው ባለሙያዋ ለዚህም አንዱ ምክንያት አብዛኛዎቹ የተቋሙ ሥራዎች ከከተማ ውጭ መሆናቸውን ተከትሎ ሴት መሃንዲሶች ርቆ የመሄድ ፍላጎት ማጣት እንደሆነ ታነሳለች:: እርሷም ወደ ጣቢያው ተመድባ ከመምጣቷ በፊት ተመሳሳይ ስጋት አድሮባት እንደነበር ጠቅሳ አሁን ግን ከአካባቢውና ከሙያው ጋር ያደረገችው ልምምድ በጣቢያው ውስጥ ደስተኛ ሆና ለመሥራት እንዳበቃት ታስረዳለች::

ካደገችበት አካባቢ አንጻር አሁን እየሠራች ያለችበት ቦታ ከፍተኛ ሙቀት እንዳለው የተናገረችው ወጣቷ መሃንዲስ ተልዕኮዋን ለመፈጸም አስቸጋሪውን የአየር ጸባይ ተቋቁማ ተጠቃሽ ሥራ እየሠራች እንዳለችና ሴቶች ከወንዶች ያልተናነሰ በተመደቡበት ሁሉ መሥራት እንደሚችሉ እርሷ ምሳሌ መሆን እንድምትችልም ትገልጻለች::

እንደ ግልገል ጊቤ 2 ኃይል ማመንጫ ጣቢያ ከተሠሩ የጥገና ሥራዎች ግንባር ቀደሙ የተርባይኖች ጥገና ነው የምትለው መልካም ፤ ከተጠገኑት ተርባይኖች በአንዱ ላይ በተደረገው የኖዝል ቅየራ መሳተፏንና በዚህ የጥገና ሂደትም በርካታ ልምድ መቀስሟን ትናገራለች፤ በቀጣይ ለሚደረገው ሌላኛው የተርባይን ጥገናም በቅድመ ዝግጅት ሥራዎች ስታሳተፍ እንደቆየችና ለኖዝል ገጠማውም እራሷን እያዘጋጀች እንደምትገኝ ታስረዳለች::

ወጣት ሳሙኤል ንጉሤ የቴክኒክና ሙያ ትምህርቱን አጠናቆ በ2010 ዓ.ም የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይልን የተቀላቀለ ተስፈኛ ባለሙያ ነው:: ተቋሙ የስድስት ወር ሥልጠና ከሰጠው በኋላ ግልገል ጊቤ 2 ኃይል ማመንጫ ጣቢያ በኦፕሬሽን እና ሜንቴናንስ ቴክኒሻንነት ተመድቦ በመሥራት ላይ ይገኛል:: አሁን ላይ በአመዛኙ የኦፕሬሽን ሥራ እንደሚሠራ የተናገረው ሳሙኤል ስካዳ ሲስተምን በማንበብ በማሺኖች ላይ ቁጥጥር የማድረግ፣ ኃይል የመጨንና የመቀነስ ሥራዎችን ይሠራል:: እነዚህም የዕለት ተዕለት ተግባራቱ መሆናቸውን ይጠቅሳል::

ሳሙኤል ከሥራው ጎን ለጎን ጣቢያው ያመቻቸለትን የትምህርት እድል ተጠቅሞ በዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ በቅዳሜና እሁድ መርሃ-ግብር የምህንድስና ትምህርቱን እየተማረ ይገኛል:: በአሁኑ ሰዓት የኤሌክትሪካል ኮምፒዩተር ኢንጂነሪንግ የሶስተኛ ዓመት ተማሪ እንደሆነም ይገልጻል:: እየተማረ ያለውን የንድፈ ሃሳብ ትምህርት ከተግባር ጋር እያዋሃደ ለመረዳት በጣም እንደረዳው ይናገራል:: ጣቢያው የትምህርት እድል ስላመቻቸለትና የሥራ ባልደረቦቹም ትምህርት ባለው ቀን ሥራውን ሸፍነው ስለሚሠሩለት ከፍ ያለ ምስጋና ማቅረብ እንደሚፈልግ ይገልጻል:: በትምህርትና በልምድ እራሱን አብቅቶ እናት መሥሪያ ቤቱን ለማገልገል ቁርጠኛ ስለመሆኑም ይናገራል::

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ